የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ- ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 33
ADDIS ABABA- 28th April, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፮/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ለሁለተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...ገጽ ፫ሺ፺፩

CONTENTS

**Proclamation No. 446/2005**

International Development Association Credit Agreement for financing Second Roads Sector Development Support Project Ratification Proclamation ........ Page 3091

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፮/፲፱፻፺፯

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፲ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አሥር ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፲ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፮/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 446/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount not exceeding SDR 110,000,000 (one hundred ten million SDR) for financing Second Roads Sector Development Support Project, was signed in Addis Ababa on 10th March 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 14th day of April, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for financing Second Roads Sector Development Support Project Ratification Proclamation No. 446/2005."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፲ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ቁጥር 3989ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፲ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አሥር ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Credit Agreement No. 3989ET signed in Addis Ababa on the 10th March, 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 110,000,000 (one hundred ten million Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall inter into force on the 28th day of April, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of April, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**